# ለጎሬቤት ችግር ዋይታ፣
# ለወገን ስቃይ ዝምታ!
# ምክንያቱ ምን ይሆን?

ባለፈው ወር የኢህአደግ መንግስት በፓርላማው አማካይነት ስለ ኤርትራውያን ንብረት መመለስ ጉዳይ አጀንዳ አስይዞ እንዲመለስላቸው ማስወሰኑን ሰምተናል። ከኔ ጀምሮ ብዛት ያለው ወገን በዚሁ ድርጊት በጣም ተገርሟል። ንብረቱን ለተወሰደው ወገን መመለስ ሳይሆን የገረመን በተጋዳኝ መልኩ በኤርትራ ያሉ ወገኖች ከንብረታቸው መወረስ አልፎ የተገደሉ፣ የታሰሩ፣ የትም ተወሰደው የተጣሉና እስከ አሁንም መከራና ግፍ እየተቀበሉ መሆናቸው እየታወቀ ዝም መባሉ ነው። በኤርትራ ምድር እስከ አሁንዋ ደቂቃ መከራና ስቃይ እየተቀበለ ላለው ወገን (በተለይም የትግራይ ተወላጆች) ለይምሰል እንኳ ምክር ቤቱ ላንድፍታ አለመነጋገሩ አሁንም ከመግረም አልፎ እጅግ ያንገበግባል። በውነት የኤርትራውያን በኢትዮጵያ መንግስት መበደል በወገናችን በኤርትራ ከደረሰውና አሁንም ከሚደርሰው በደል በልጦ ነው የወገኖቻችን በደልና ስቃይ በዝምታ እንዲታለፍ የተመረጠው ያስብላል። ወይስ እንደተለመደው ቅድምያ ለጎሬቤት ወገኖች የምትባለው መዝሙር አሁንም ለመድገም?

አንዳንድ የመንግስት ደጋፊዎችና የዋሃን አሁን ያለው የኤርትራ መንግስቱ እንካንስ ለ ኢትዮጵያውያን ሊያዝን፣ ለዜጎቹ እንኳ ምህረት የለሽ የሆነ አውሬ መንግስት ነውና የኢትዮጵያ መንግስት ጉዳዩ አነሳው አላነሳው የሚፈይደው የለም ይላሉ። ይህ አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑን ለማስረዳት አይከብድም። ዋና የመንግስት ሃላፊነት እኮ የዜጎች መብት በየትም አለም ይኑር ማስከበር ነው። አንድ ዜጋ ችግር ሲደርስበት መንግስት እስከ ሃይል የመጠቀም ደረጃ ሁሉ ሊሄድ ይችላል። ሳያመች ሲቀር ደግሞ ከሚመለከታቸው አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመሆን ያገሩን ዜጋ ከሚደርስበት ስቃይና መከራ እንዲገላገል አበርትቶ ይሰራል። ያለው መንግስት ግን ከዚሁ በላይ ከተጠቀሰው የመንግስት ግዴታና ተግባር ውጭ ለጎሬቤት አገር ዜጎች መብት ለማስከበር የተቻለውን ሲያደርግ ለወገኖቹ ግን ዝምታ ነው የቸረው። የኢትዮጵያውያን ጥያቄ ደግሞ ይህ መንግስት በአካል ባይደርስላቸውም “የወገናችን ስቃይ ይሰማናል” የሚለው ቃል እንኳ ፓርላማው በመግለጫ መልክ ድምጹን ቢያሰማ ካንጀት ካለቀሱ ዕንባ አይገድም በሆነ ነበር። አንድ ሰው በጠና ታሞ ሆስፒታል ገብቶ ወገን የሚጠይቀው ጠያቂው የማዳን ሃይል ስላለው ሳይሆን ደንቡና ስርዓቱ እንደዛው ስለሆነ ነው እንጂ የታማሚው ሰው ህይወትዋ በእ/ሄር እጅ ነው ያለችው። ይህንን ላብነት የጠቀስኩት ዝምታው ትክክል አይደለም ምክንያቱም በታሪክም ይስጠይቃል፣ በባህላችንም ነውር ነው ለማለት ነው።

ጉፍዓን ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ! “እንደ ወንድ ተዋግተህ ያላዳንካት አገር እንደ ሴት አልቅስላት” የሚለው የድሮ ፊሊፕ በመከተል አቅሜ መፃፍ ሆነና የኢትዮጵያ አምላክ ካላችሁበት ምድራዊ ሲዖል እንድትገላገሉ ይርዳችሁ ከማለት ያለፈ ነገር ሌላ የለኝም።

በመጨረሻም እ/ሄር ፈራጅ ነውና ለሚገፍዋችሁ ፍርዱን አይጉደልባቸው በማለት ለናንተው ያለኝ የሃዘን ስሜት ስገልፅ ካንጀት ነው! ።

ወገናችሁ ኢትዮጵያዊ

ሃይለ ደስታ